# ሚያዚያ 8 ቀን 2011 ዓ.ም

## ርዕሰ ዜና

- በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሥራ ፍለጋ ላይ እንደሚንከራተቱ የዓለም ባንክ በዘገባው ገልጿል
- ተፈናቃይ ዜጎች በሚኖሩባቸው 142 ወረዳዎች ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲቱት ገለጸ
- መጋቢት 28 ቀን ከጂቡቲ ወደ ሳኡዲ አረቢያ ስትጓዝ የነበረችው ጀልባ በመገልበጧ 70 ኢትዮጵያውያን ህይወታቸው ያለፈ መሆኑ ታውቋል
- ሰኞ ከጋምቤላ ማረሚያ 92 እስረኞች ያመለጡ መሆናቸው ተነግሯል
- የሱዳንን ህዝባዊ አመጽ በመምራትና በማስተባበር ላይ የሚገኘው የሱዳን ፕሮፌሽናል ካውንስል ጊዜያዊው ወታደራዊ አስተዳደር ከሲቪል በተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት እንዲተካ ጠይቋል

## ዝርዝር ዜናዎች

➢ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሥራ ፍለጋ ላይ እንደሚንከራተቱ የዓለም ባንክ ባወጣው ዘገባ ገልጿል። አሁን ባለው የአገዛዙ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በየዓመቱ ለሁለት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ለመፍጠር የማይቻል መሆኑን የሚገልጹት የባንኩ ባለሙያዎች በአጠቃላይ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ በተለይም በእርሻና በትምህርት እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች መሰረታዊ የፖሊሲ ለውጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ከእነዚህም ውስጥ የተለዩ ኢንዱስትሪዎችን በገጠር ማቋቋም፤ የቁጥጥር ሥርዓትን ማሻሻል የሚሉ ይገኙባቸዋል። ታዛቢዎች በዘር ላይ የተመሰረተው ጸረ ሕዝብ አገዛዝ ካልተወገደ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ይላሉ።

➢ በመጭው የበልግና የክረምት ወራት በርካታ ተፈናቃዮች የሚኖርባቸው አካባቢዎች በሚከሰት ጎርፍ ተፈናቃዮች የጤናና የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሟቸው እንደሚችል የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲቱት ገለጸ። ተፈናቃይ ዜጎች በሚኖሩባቸው 142 ወረዳዎች ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ

መሆናቸውን ተቋሙ የገለጸ ሲሆን እነዚህ ተፈናቃዮች ለሚገኙባቸው አካባቢዎች ማስጠንቀቂያ የላከ መሆኑ ይፋ አድርጓል። መጭውን የበልግና የክረምት ወራትን ተከትሎ በጎርፍ አደጋ ምክንያት ተጨማሪ የዜጎች መፈናቀል ሊደርስ እንደሚችልም ስጋት ያለው መሆኑን ኢንስቲትዩት ገልጿል። በንጽህና ጉድለት ተላላፊ በሽታ በወረርሽኝ መልክ ሊከሰት እንደሚችልም አስጠንቅቋል። በግጭቶች ምክንያት የወደሙ የጤና ጣቢያዎችን መልሶ ለማቋቋም ሥራ መጀመሩን ተቋሙ ገልጿል። በዝናም ወቅት የመንገድ መዘጋት ሊያጋጥም ስለሚችልም ለህክምና የሚሆኑ ቁሳቁሶች ከወዲሁ መዘጋጀት እንዳለባቸው አሳስቧል።

- ቅዳሜ መጋቢት 28 ቀን ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሳኡዲ አረቢያ ስትጓዝ የነበረችው ጀልባ በመገልበጧ 70 ኢትዮጵያውያን ህይወታቸው ያለፈ መሆኑ ታውቋል። ከሟቾቹ ውስጥ ስድሳ የሚሆኑት በትግራይ የአጽቢ ወንበራታ ወረዳ ተወላጆች መሆናቸው ተነግሯል። በአጽቢ ወንበራታ ወረዳ የሚኖሩ የ43 ሟቾች ወላጆች መርዶው የተነገራቸው መሆኑንና በጋራ በቤተ ክርስቲያን የፍትሃት ስርዓት እንደተደረገላቸው ተገልጿል። በመላ ኢትዮጵያ በአስከፊ አገዛዝና በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ወደ ውጭ  የሚወጡት  ወጣቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ መሄዱ ሲነገር ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ካልተወገደ በስተቀር ችግሩ አይወገድም የሚሉ በርካታ ናቸው።

- ሰኞ  ከጋምቤላ ማረሚያ 92 እስረኞች  ያመለጡ መሆናቸው ተነግሯል። በመጠጥ ውሃ ሽሚያ በሁለት ግለሰቦች መካከል የተነሳውን ግጭት ለማብረድ ስድስት የጸጥታ ኃይሎች ሙከራ በሚያደርጉበት ወቅት እስረኞቹ ጠባቂዎችን በመደብደብ በዋናው በር በኩል አምልጠዋል ተብሏል። ወንጀለኞቹ ባመለጡበት ወቅት የተኩስ ድምጽ ሲሰማ መቆየቱን ነዋሪዎች ለዜና ምንጮች የገለጹ ሲሆኑ ከአመለጡት እስረኞች ውስጥ ብዙዎች በነፍስ ግድያና በሌሎች ወንጀሎች የተያዙ እንደነበሩ ባለሥልጣኖች ገልጸዋል።

- የሱዳንን ህዝባዊ አመጽ በመምራትና በማስተባበር ላይ የሚገኘው የሱዳን ፕሮፌሽናል ካውንስል ሰኞ ዕለት በሰጠው መግለጫ የቀድሞ አገዛዝ ርዝራዦች አሁንም በሥልጣን ላይ ያሉ መሆናቸውን ጠቅሶ በአሁኑ ወቅት የተቋቋመ ጊዜያዊ የወታደራዊ አስተዳደር ከሲቪል በተውጣጣ ጊዜያዊ መንግሥት እንዲተካ ጥያቄውን አድሶ ገልጿል። ህዝባዊ እንቅስቃሴውን እየመራ ያለው አካል የአገሪቱ ሕገ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱና የገዥው መደብ ፓርቲ የሆነው ብሔራዊ የኮንግሬስ

ፓርቲ እንዲፈርስ ጥያቄ አቅርቧል። የህዝቡ ተጋድሎና አብዮት በጀርባ በሚሸረቡ ሸሮች እየተጠናከሩ በሄዱበት ሁኔታ ግባቸውን ሊመቱ አይችሉም ብሏል።

# ሚያዚያ 7 ቀን 2011 ዓ.ም

## ርዕሰ ዜና

- በሥልጣን ላይ ያሉት ጠባብ ሹሞች በተጨባጭ የኦነግ ወይም የጥበትና ግንጠላ ተልዕኮ አስፈጻሚዎች መሆናቸውን እያስመሰከሩ ነው
- ሹሞቹ የመጡት ያለውን ዘረኛ እቅድ ከግብ ለማድረስ ሆኖ ሳለ ለሀገር አንድነት የቆሙ ይመስል፤ "አልቻሉበትም" የሚለው ዕውነታውን አለመናገር ነው
- በድሬደዋ ከተማ ከጥቂት ቀናት በፊት የተነሳው ግጭት ተባብሶ የቀጠለ መሆኑ ተነግሯል
- በወሎ ዩኒቨርስቲ በተማሪዎች መካከል የነበረው ውጥረት በሽምግልና የተፈታ መሆኑን የዩኒቨርስቲው ባለሥልጣኖች አስታውቀዋል
- የጅማ ዩኒቨርስቲ የመጨረሻ ዓመት የህክምና ተማሪዎች የሥራ ማቆም አድማ ካደረጉ አንድ ሳምንት ሆኗቸዋል
- በሰሜን ተራሮች የተነሳው እሳት እስካሁን ከትናንት ጀምሮ በሄሊኮፕተር የታገዘ የማጥፋት ሥራ ቢከናወንም ውጤቱ ደካማ ነው እየተባለ ነው
- በአገዛዙ ደረጃ የሚወሰነው የቋሚ የውጭ ምንዛሬ ልውውጥ አብቅቶ ምንዛሪው በገበያ ዋጋ ላይ እንዲወሰን አገዛዙ እቅድ መያዙ ተዘገበ

## ዝርዝር ዜናዎች

- በሥልጣን ላይ አለን የሚሉት ጠባብ ሹሞች በተጨባጭ የኦነግ ወይም የጥበትና ግንጠላ ተልዕኮ አስፈጻሚዎች መሆናቸውን በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገሮችም እያረጋገጡ ነው ተብሏል። በፈረንሳይ አምባሰደር ብለው የሾሙት ግለሰብ በፈረንሳይ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ለመተዋወቅ በሚል በኤምባሲው ያሳየው ትርኢት የሾሙትን ሰዎች ደባ የሚያጋልጥ ነው በሚል ተተችቷል። የኤምባሲው አዳራሽ የኦነግን ባንዲራ በለበሱ ስደተኞች የተጨናነቀ ከመሆኑም በላይ ይህ በፈረንሳይ የነጻ ትምህርት እድል ተሰጥቶት የተማረ ግለሰብ የሚቀበላቸውን እንግዶች በአማርኛ ለማናገርም አለመፈለጉን አሳይቶ ነበር ተብሏል። በመጨረሻም ያው ንግግሩን ፈረንሳይ በተደባለቀበት አማርኛ ካሰማ በኋላ እንጸልይ ሲል ያው አገዛዙ እያፈናቀላቸው ላሉትና ለገደላቸው ዜጎቻችን ባይሆንም የሃይማኖት ተወካዮች ያላቸውን ካቀረበ በኋላ የገዳም ተጠሪ ብሎ ማቅረቡን በስፍራው የነበሩ ዜጎች ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ሳይሆን የኦነግ ጽህፈት ቤት መስሎ የዋለው

በፓሪስ ያለው ኤምባሲ ከተቋቋመ ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም ሀገራችንን ለፈረንሳይ ኩባንያዎች ከማመቻቸትና የወያኔን ጥቅም ከማስጠበቅ አልፎ ምንም ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ሲሰራ ሳይታይ ዓመታት አልፈውታል ተብሏል።

- ሹሞቹ የመጡት ያለውን ዘረኛ እቅድ ከግብ ለማድረስ ሆኖ ሳለ ለሀገር አንድነት የቆሙ ይመስል አልቻሉበትም በሚል የሚከሷቸው ክፍሎች ተሳስተዋል ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ተችተዋል ። ሹሞቹ ከአሜሪካና አረቦች (ግብጽንም ጨምሮ) እንዲሁም ከሻዕቢያ ተመሳጥረው ይዘውት የመጡት ዕቅድ የራሳቸውን ድርጅትና ብሔር የበላይነት ማስፈንና፤ ሌላውን ሕዝብ ደግሞ ማፈናቀልና መፍጀት ስለነበር ይህን በሚገባ እያከናወኑ ናቸው ያሉት እነዚህ ታዛቢዎች የአሜሪካ ጋዜጦች በሹሞቹ ላይ የሚያሰሙት ወቀሳና አሁንም እጥፍ ዘርጋ እያሉ ሹሞቹን የሚደግፉት ሻለቃዎችና ምሁር ተብዬዎች የሚያሰሙት ቅሬታ ቦታና ቅንነት የለውም ብለዋል። ሹሞቹ ለመጡበት ዓላማ የሚበጇቸውን ጽንፈኞችና ስግብግብ ዘረኞች ጠርተው በሕዝብ ላይ ያሰማሩ ሲሆን አሁንም ይህን ጸረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴያቸውን የሚቀንሱና የሚያቆሙ ይሆናሉ ብሎ መመኘት ሞኝነት ነው ብለዋል። ሹሞቹ ማንነታቸውን በሕዝብ ስም አጥበውና ጭምብላቸውንም አውልቀው ያሳዩ ስለሆነ ከእባብ ዕንቁላል ርግብ፤ ከወያኔ ተለጣፊዎችና ዘረኞች ሀገር ወዳድነትን መጠበቅ ከንቱ ነው ያሉት ክፍሎች በትግል ሹሞቹን ማስወገድና ጽንፈኞቹንም ጥግ ማስያዝ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል። ወያኔ በሁኔታው ተጠቅሞ ወደ ቦታው ሙሉ በሙሉ ለመመለስ አሜሪካንን እየተማጸነ ነው ሲባል ሹሞቹን በምርጫ ሊያጅቡ የተነሱት ደግሞ ከፖለቲካው ምድረበዳ መውጣት እንዳልቻሉም እየታየ ነው ተብሏል።

- በድሬደዋ ከተማ ከጥቂት ቀናት በፊት የተነሳው ግጭት ተባብሶ የቀጠለ መሆኑ ተነግሯል። አርብ በተከሰተው ግጭት በዜጎች ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ግጭቱ በተለይ ፖሊስ መሬት በሚባለው ቦታ ቅዳሜና እሁድ መቀጠሉና አሁንም ያልበረደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በከተማዋ ወጣቶችና የጸጥታ ኃይሎች መካከል የሚፈጠረው ግጭት በርካታ ሰዎችን የአካል ጉዳተኛ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ለብዙዎቹ መፈናቀል ምክንያት ሆኗል ተብሏል።

- በወሎ ዩኒቨርስቲ በተማሪዎች መካከል የነበረው ውጥረት በሽምግልና የተፈታ መሆኑን የዩኒቨርስቲው ባለሥልጣኖች አስታውቀዋል። የዩኒቨርስቲው ኃላፊዎች፤ የአገር ሽማግሌዎችና

የሃይማኖት አባቶች ባካሄዱት የተባበረ ተከታታይ ጥረት በሁለት ጎራ ተከፍለው እርስ በርሳቸው ግጭት ፈጥረው የነበሩትን ተማሪዎች ለማስታረቅ የተቻለ መሆኑ ታውቋል።

- የጅማ ዩኒቨርስቲ የመጨረሻ ዓመት የህክምና ተማሪዎች የሥራ ማቆም አድማ ካደረጉ አንድ ሳምንት ሆኗቸዋል። ተማሪዎቹ ከጠየቋቸው ጥያቄዎች መካከል ለጤና ባለሙያዎች የተሟላ የጸጥታ ጥበቃ እንዲመደብ፤ ተገቢ ውክልና እንዲሰጣቸው፤ የጤና ባለሙያዎች የሥራ ሰዓት እንዲስተካከል፤ ሥራቸው በውል ተለይቶ ተግባራዊ እንዲሆን፤ የመድኃኒትና የሌሎች የህክምና ቁሳቁሶች የተሟሉ እንዲሆኑ የሚሉ ይገኙባቸዋል። የኢትዮጵያ ወጣት ሀኪሞች ማህበርና የህክምና ተማሪዎች ማህበር ከተማሪዎቹ ጎን የሚቆሙ መሆናቸውን ገልጸው አጋርነታቸውን አሳውቀዋል።

- በሰሜን ተራሮች የተነሳው እሳት እስካሁን በቁጥጥር ስር ያልዋለ መሆኑ ተነገረ። ከትናንት ጀምሮ በሄሊኮፕተር የታገዘ እሳቱን የማጥፋት ሥራ ቢከናወንም የተፈለገውን ያህል ውጤት ማስገኘት አለተቻለም ተብሏል። በሥራ ላይ የዋለችው አንድ ከእስራኤል የተገኘች ሄሊኮፕተር ብቻ ስትሆን የምትይዘው ነዳጅ ለሶስት ሰዓት ብቻ የሚያሰራት መሆኑና እንዲሁም ውሃ ለመቅዳት ወደ ደባርቅ አካባቢ ስትመላለስ የሚጠፋው ጊዜ ሰፊ በመሆኑ እሳቱ ተመልሶ የሚቀጣጠልበት እድል እያገኘ ነው ፤ እሳቱ በአሁኑ ወቅት ወደ ቆላማው የፓርኩ ክፍል እየተዛመተ በመሆኑ እያየለ ነው ትብሏል። እስካሁን 400 ሄክታር የሚሆን ቦታ ላይ የሚገኝ እጽዋትን እንዳወደመ ተነግሯል።

- በአገዛዙ ደረጃ የሚወሰነው የቋሚ የውጭ ምንዛሬ ልውውጥ አብቅቶ እንደሌሎቹ አገሮቹ የውጭ ምንዛሬው ዋጋ በገበያ ላይ እንዲወሰን አገዛዙ እቅድ መያዙ ተዘገበ። ይሁን እንጅ ይህ አሰራር በቂ ዝግጅት ሳይደረግበት የአንድ ወር የመድኃኒትና የነዳጅ እቃዎች ለማስመጣት የሚያስችል እንኳ የውጭ ምንዛሬ በሌለበት ሁኔታ በገበያ ላይ እንዲወሰን ማድረግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ የሚያስከትል መሆኑን የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ያስጠነቅቃሉ። ባለሙያዎቹ የውጭ ምንዛሪው ተመን ገበያ ላይ እንዲወሰን ወደ እሚያስችል አሰራር ለመግባት አገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ክምችት መያዟ በቅድሚያ መሟላት ያለበት መሆኑን ገልጸው ይህ በሌለበት ሁኔታ ፖሊሲው ተግባራዊ ቢደረግ የሚያስከትለውን የአገሪቱን የዋጋ ግሽበትም ሆነ እያሻቀበ የሚሄደውን የብድር መጠን መቆጣጠር አይቻልም ብለዋል።